# ማውጫ

## የሥራ ዓይነት ምደባ መለያ ኮድ ዝርዝር

ገጽ


መግቢያ ........ 1
ዋና ክፍል 1 - ሕግ አውጭዎች፣ ከፍተኛ ባለስልጣኖችና ሥራ አስኪያጆች ........ 2
ዋና ክፍል 2 - ኘሮፌሽናሎች ........ 2
ዋና ክፍል 3 - ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ኘሮፌሽናሎች ........ 4
ዋና ክፍል 4 - የጽሕፈትና ተመሣሣይ ሠራተኞች ........ 5
ዋና ክፍል 5 - የአገልግሎት የሱቅና የገበያ ሽያጭ ሠራተኞች ........ 6
ዋና ክፍል 6 - የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎችና ዓሣ አስጋሪዎች ........ 6
ዋና ክፍል 7 - የዕደ ጥበብና ተመሳሳይ ሠራተኞች ........ 7
ዋና ክፍል 8 - የማምረቻ መሣሪያዎች ኦኘሬተሮችና ገጣጣሚዎች ........ 8
ዋና ክፍል 9 - ዝቅተኛ ሥራ ሠራተኞች ........ 9
ዋና ክፍል 0 - የጦር ኃይል አባላት ........ 10


## የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት/የኢንዱስትሪ/የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ምደባና መለያ ኮድ ዝርዝር


መግቢያ ........ 10
ዋና ክፍል ለአንድ - ግብርና፣አደን፣ደን ሀብትና ዓሣ ማስገር ........ 11
ዋና ክፍል ሁለት - ማዕድን፣ ድንጋይና አሸዋ ማውጣት ........ 11
ዋና ክፍል ሦስት - ማኒፋክቸሪንግ ........ 12
ዋና ክፍል አራት - ኤሌክትሪክ፣ጋዝና ውሃ አቅርቦት ........ 16
ዋና ክፍል አምስት - ኮንስትራክሽን ........ 17
ዋና ክፍል ስድስት - የጅምላና ችርቻሮ ንግድ፣መኪናዎች፣ሞተር ........ 17
ብስክሌቶች፣የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች መጠገን ........ 18
ዋና ክፍል ሰባት - ሆቴሎችና ምግብ ቤቶች ........ 19
ዋና ክፍል ስምንት - ትራንስፖርት፣የመጋዘን አገልግሎትና መገናኛ ........ 19
ዋና ክፍል ክፍል ዘጠኝ - የፋይናንስ/የገንዘብ እንቅስቃሴ/ዝውውር/ ........ 20
ዋና ክፍል አሥር - የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ኪራይና ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎች ........ 21
ዋና ክፍል አሥራ አንድ- የመንግስት አስተዳደርና የመከላከያ፣
የማህበራዊ ዋስትና/ጡረታ/አገልግሎት ........ 21
ዋና ክፍል አሥራ ሁለት- የትምህርት፣የጤናና ማህበራዊ አገልግሎት ........ 21
ዋና ክፍል አሥራ ሦስት - ሌሎች የማህበራዊ፣የባህል የመዝናኛ፣
የግልና የቤተሰብ ግልጋሎቶች ........ 22
ዋና ክፍል አሥራ አራት- ቅጥር ሠራተኛ ያሏቸው ቤተሰቦች ........ 22
ዋና ክፍል አሥራ አምስት - የውጭ ድርጅቶች ........ 23

# የሥራ ዓይነት ምደባ መለያ ኮድ ዝርዝር

*መግቢያ*

*የሥራ ዓይነት ምደባ የሰው ኃይልን በሚመለከት ልዩ ልዩ መረጃዎችን በማስገኘት ፕላን ለማውጣት ይረዳል፡፡ የሰው ኃይልን ለመገመት፣ የትምህርትና የማሠልጠኛ ፕሮግራሞችን ለማውጣት፣ ለአስተዳደር አገልግሎት፣...ወዘተ. በአጠቃላይ ከፍተኛ ጥቅም ያለው መረጃን ያስገኛል፡፡*

*የአንድ ግለሰብ የሥራ ዓይነት የሚመደበው ግለሰቡ በድርጅቱ ውስጥ በሚሠራው በአንድ በተወሰነ ወይም በዋነኛ ሥራው ነው፡፡ ለምሳሌ በአንድ ሆስፒታል በታይፒስትነት የምትሠራ ግለሰብ ሥራሽ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ በዓምድ 31 ታይፒስት ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ይህ የሥራ ዓይነት የጽሕፈትና ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ሠራተኞች ምደባ ውስጥ ስለሆነ ትክክለኛውን ኮድ ከተሰጠው የሥራ ዓይነት መለያ ኮድ ዝርዝር ከገጽ 5 ከዋና ክፍል 4 ከንዑስ ክፍል 41 በመምረጥ በካርድ ኮለሞቹ ኮድ 411 ይሞላል፡፡*

*የግብርና ዕውቀት ያለው በግል ለሌላ በግብርና ለተሠማራ ግለሰብ ሥራህ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ የግብርና ዕውቀት ያለው የግል ገበሬ ተብሎ ተሞልቶ ከሆነ ትክክለኛውን ኮድ ከተሰጠው የኮድ ዝርዝር ከገጽ 7 ከዋና ክፍል 62 በመምረጥ ኮድ 621 በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል፡፡*

*በዓምድ 31 የዋነኛ ሥራዎ ዓይነት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ፣ ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት በሙሉ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ ነገር ግን ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ ሆኖ ዓምዱ ያልተሞላላቸው ግለሰቦች ቢገኙ መረጃው መሞላት ሲገባው ያልተሞላ መሆኑን ለማመልከት ኮድ 999 በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል፡፡*

# ዋና ክፍል 1- ሕግ አውጭዎች፣ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ሥራ አስኪያጆች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች አብዛኛዎቹ ተግባራት ፖሊሲን መቅረፅና መወሰን እንዲሁም ሕጎችንና የሕዝብ መተዳዳሪያዎች፣ አፈፃፀማቸውን መከታተል፣ መንግስትን መወከልና እንደ መንግስት መሥራት፣ የኢንተርፕራይዞችንና የመምሪያዎችን ተግባራት ማቀድ፣ መምራትና ማስተባበርን ያጠቃልላሉ:: ዋና ክፍሉም የማዕከላዊ መንግሥት፣ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ ሕግና ደንብ አውጭዎችና አስፈጻሚዎችን፣ የድርጅቶችን አመራር አካላትና የዋና ክፍል የክፍልና የአገልግሎት ኃላፊዎች ያጠቃልላል:: በዚህ ዋና ክፍል ውስጥ የተለያዩ የትምህርትና የሙያ ደረጃ ያላቸው አብረው ይገኛሉ::

## 11. ሕግ አውጭዎችና ከፍተኛ ባለሥልጣናት

111 ሕግ አውጭዎች
/የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ ምክር ቤት ሊቀመናብርት፣ የፓርላማ ወይም ሸንጎ አባላት፣ ከሕግ ማውጣትና ማስፈጸም ጋር ግንኙነት ያላቸው ልዩ ፀሐፊዎች/

112. የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት
/የብሔራዊ፣ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ ምክር ቤት አባላት፣ አምባሳደሮች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ሬጅስትራሮች/

113. የቀበሌ አመራር አካላትና የጎሣ መሪዎች
/የከተማ የቀበሌና ከፍተኞች፣ የገጠር ገ/ማህበራት አመራሮችና የጎሣ መሪዎች/

114. የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች፣ የአሠሪዎች፣ የሠራተኞች፣ የሙያና የራሳቸው የሆነ የኢኮኖሚ ፍላጎት ያላቸው ማሕበራት፣ የሰብዓዊና መሰል ድርጅቶች ከፍተኛ ባለስልጣኖች /ፕሬዝዳንቶች፣ መሪዎችና የአመራሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት/

## 12. ሥራ አስኪያጆችና መምሪያ ኃላፊዎች

121. መንግሥታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ትላልቅ የምርት ማምረቻና አገልግሎት መስጫ ምሳሌ:- የትራንስፖርት፣ የኮንስትራክሽን፣ የትምህርት፣ የጤና ...ወዘተ አገልግሎት መስጫ) ድርጅቶችና ተቋማት፣ ዋና ሥራ አስኪያጆች (ዋና ኃላፊዎች)፣ ሥራ አስኪያጆችና የመምሪያ ኃላፊዎች፣ ዋና ፀሐፊዎች፣ የኮሌጆች፣ የተቋማትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተሮች እዚህ ይጠቃለላሉ::

## 13. የሥራ ኃላፊዎች፣ የዋና ክፍል፣ የክፍልና የአገልግሎት ኃላፊዎች

131. የሥራ ኃላፊዎች፣ የዋና ክፍል፣ የክፍልና፣ የአገልግሎት ኃላፊዎች፣ (መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባለሆኑ መለስተኛ ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች፣ በትላልቅና በመለስተኛ ድርጅቶች የዋና ክፍል፣ የክፍልና የአገልግሎት ኃላፊዎች የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ዳይሬክተሮች) ኮንትራክተሮች

132. የአነስተኛ የግል የጅምላና የችርቻሮ ንግድ፣ የምግብ ቤቶችና ሆቴሎች ባለቤቶችና የሥራ ኃላፊዎች፣ እንዲሁም ሌሎች በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የአነስተኛ የግል የንግድና አገልግሉት መስጫ ድርጅቶች ኃላፊዎች በዚህ የሚጠቃለሉ ሲሆን፣ እነዚህ ባለሙያዎች በአብዛኛው የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ የማቀድ፣ የማስተባበርና የመምራት ተግባርን የሚያከናውኑ ናቸው::

# ዋና ክፍል 2

## ፕሮፌሽናሎች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች ተግባራቸው፣ በፊዚካል፣ በሕይወት፣ በማህበራዊ ሳይንስና በሰብዓዊ ትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ የዩኒቨርስቲ ዲግሪ ወይም ተመሣሣይ የሆነ የትምህርት ደረጃ የሚጠይቁ የስራ ዓይነቶች ናቸው:: በዋና ክፍሉ የሚካተቱ ተግባሮችም፣ ያለውን የዕውቀት ክምችት ማዳበርና ማሳደግ፣ ሳይንሳዊ ፅንሰሃሳቦችንና መላምቶችን በመጠቀም ምርምሮችን ማካሄድ፣የምርምር ውጤት የሆኑትን ግኝቶች በሥራ ላይ የማዋልና የማስተማር፣ሌሎች ሙያን የሚጠይቁ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስጠት ናቸው::

### 21. የፊዚካል ሳይንስ፣ የማቲማቲክስ፣ የምሕንድስና ሳይንስ ፕሮፌሽናሎች

211. ፊዚሲስቶችና የስነከዋክብት ተመራማሪዎች፣ ኬሚስቶች፣ ሜትሮሎጂስቶች፣ ጂኦሎጂስቶች፣ ጂኦፊዚስቶችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች
212. ማቲማቲሽያኖች፣ ስታቲስቲሽያኖችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች የመድህን ዋስትና ተንታኞችን፣ አክችዋሊስትስ፣ ዲሞግራፊሮችን ያጠቃልላል
213. የኮምፒዩተር ፕሮግራመሮችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች፣ ኮምፒውተር ሲስተም ድዛይነሮችንና አናሊስቶችን፣ የኮምፒውተር ሲስተም ኢንጂነሮችንና የዳታ ቤዝ አድሚንስትሬተሮችን ያጠቃልላል
214. አርክቴክቶች፣ ኢንጅነሮችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች የሲቪል፣ የኤሌክትሪክ፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ ሜካኒካል፣ ኬሚካል፣ የማዕድን ሥራ መሐንዲሶችና የቅየሳና የካርታ ሥራ ፕሮፌሽናሎች

### 22. የሕይወት ሳይንስና የጤና ፕሮፌሽናሎች

221. አግሮኖሚስቶች፣ ባዮለጂስቶች፣ ፋርማኮሎጂስቶችና የመሳሰሉት የደንና የአፈር ተመራማሪዎችን፣ በታኒስቶችን፣ ኢኮሎጂስቶችን፣ ዙኦሎጂስቶችን፣ ፓቶሎጂስቶችን፣ ባዮኬሚስቶችንና ባዮፊዚስቶችን፣ አናቶሚስቶችንና መሰል ባለሙያዎችን ያጠቃልላል::

222. የሕክምና ዶክተሮች፣ ዴንቲስቶች፣ ፋርማሲስቶች፣ የእንስሳ ሕክምና ዶክተሮችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች <u>( ነርሶችና ድሬሰሮች በዚህ አይጠቃለሉም)</u>

223. የጤና መኮንኖች፣ ስፔሻላይዝድ ያደረጉ ነርሶችና አዋላጅ ፕሮፌሽናሎች <u>(የልምድ አዋላጆችን አይጨምርም)</u>

### 23. የማስተማር ፕሮፌሽናሎች

231. የኮሌጆች፣ ዩኒቨርስቲዎችና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራን
232. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን
233. ኢንስፔክተሮች፣ የትምህርት ካሪኩለም አዘጋጆችና የመሳሰሉት (የልዩ ትምህርት: የዓይነ ስውራን፣ መስማት የተሳናቸው ...ወዘተ ካሪኩለም አዘጋጆች እዚህ ይጠቃለላሉ)

### 24. ሌሎች ፕሮፌሽናሎች

241.አካውንታንቶች፣ ኦዲተሮችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች
242.ዳኞች፣ ጠበቆችና የመሳሰሉት የወረዳ ዐቃቤ ሕግ
243.የቤተመጻሕፍት፣ የሙዚየምና የመሳሰሉት ሥራ ፕሮፌሽናሎች
244.ኢኮኖሚስቶች፣ ሶሽሎጂስቶች፣ ሂስቶሪያኖች፣ ሳይኮሎጂስቶች የሶሻል ወርክና የመሳሰሉት የሶሻል ሳይንስ ፕሮፌሽናሎች
245.የሙዚቃ የትያትር የፊልም ሥራ ፕሮፌሽናሎች፣ የስዕልና የቅርፃ ቅርፅ ሥራ፣ የጋዜጠኝነትና የፀሐፊነት ፕሮፌሽናሎች፣ ደራስያንና የመሳሰሉት
246.የሐይማኖት ፕሮፌሽናሎች/ጳጳሶች፣ ኢማሞች ...ወዘተ/

# ዋና ክፍል 3

## ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች ቴክኒካዊ ዕውቀትና የሥራ ልምድ የሚጠይቁና በአብዛኛው ከ12ኛ ክፍል በላይ በሆኑ ተቋሞች፣ ኮሌጆች፣ ...ወዘተ የሚሰጥ የትምህርት ደረጃ ወይም ተመሳሳይ የሆነ ደረጃ የሚጠይቁ ናቸው። በዋና ክፍሉ የሚካተቱት አብዛኞቹ ተግባራቶች ከፊዚካል ሳይንስ፣ ከተፈጥሮ ሳይንስና ከሶሻል ሳይንስ ጋር የተያያዙ ቴክኒካዊ ሥራዎችን ማከናወንና የማስተማር ናቸው።

31.

የም

ሕንድስናና የፊዚካል ሳይንስ ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

311. የምሕንድስናና የፊዚካል ሳይንስ ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች (የኬሚካል፣ የሲቪል፣ የኤሌክትሪካል፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የሜካኒካል፣ የማዕድን ሥራ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎችና ቴክኒሽያኖች ቀያሾች፣ የንድፍ ሥራ ባለሙያዎች፣ የሕንፃ ኢንስፔክተሮች የካርታ ሠራተኞች፣ የኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ ቴክኒሽያኖችና የመሳሰሉት)

312.

የኮምፒዩተር ኦፕሬተሮች፣ ረዳት ፕሮግራመሮችና የመሳሰሉት

313. የፎቶግራፍ፣ የድምፅ፣ የምስል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የሕክምና መሣሪያዎች ኦፕሬተሮችና የመሳሰሉት ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

314. የአውሮፕላን የአየር መቆጣጠሪያና የመርከብ ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች፣ ፓይለቶች፣ የመርከብ ነጂዎች፣ ... ወዘተ

315. የስራ ደህንነትና የስራ ጥራት ኢንስፔክተሮች፣ ለምሳሌ፣ የሕንፃና የእሳት አደጋ መከላከያ ኢንስፔክተሮች፣ የአካባቢ ጤንነት ኢንስፔክተሮች (ሳኒተሪን አይጨምርም) የምርት ጥራት ኢንስፔክተሮችና የመኪና ደህንነት ኢንስፔክተሮች

## 32. የሕይወት ሳይንስና የጤና ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

321. የግብርና፣ የአፈር፣ የደን፣ የፌርማኮሎጂ፣ የባዮኬሚስትሪ፣ የባዮሎጂ፣ የደምና የመሳሰሉት ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች (የግብርና አማካሪዎችና የግብርና የሠርቶ ማሳያ ባለሙያዎች እዚህ ይጠቃለላሉ።)

322. ነርሶች፣ የጤና ረዳቶች፣ ድሬሰሮች፣ ሳኒተሪያኖች፣ የፊዚዮቴራፒ ረዳቶች፣ የጥርስ ሕክምና ረዳቶች፣ የመነፅር ሥራ ረዳቶች፣ የፋርማሲ ረዳቶች፣ የፋርማሲስት ረዳቶች፣ የነርስ ረዳቶች፣ ሶሻል ዎርከሮችና የመሳሰሉት የከብት ሕክምና ረዳቶችና ቴክኒሽያኖች

323. የልምድ አዋላጆችና የባህል ሕክምና አዋቂዎች /በእምነት ላይ በመመርኮዝ ሕሙማንን የሚያድኑ፣ ዘመናዊ ሕክምና ሳይጠቀሙ የተለያዩ ቅጠላ ቅጠልና ሥራሥሮችን በመጠቀም ሕሙማንን የሚያክሙና በእምነት ላይ በመመርኮዝ የአእምሮና የአካል ችግሮችን የሚያክሙ /ቃልቻ፣ ጠንቋይና የመሳሰሉትን አያጠቃልልም/

## 33. የማስተማር መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

331. የአንደኛና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና የሕፃናት ማሳደጊያዎች መምህራን (የተመሳሳይ ደረጃ ት/ቤቶች ዓይነ ስውራን፣ ...ወዘተ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች)

332.
የቁስ

ት/ቤቶችና የቁርዓን ት/ቤቶች መምህራን

333. የመኪና መንዳት፣ የታይፕ ትምህርት፣ የመሳሰሉት መምህራን (የበረራ መምህራን እዚህ ይጠቃለላሉ፡፡)

## 34. ሌሎች መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

341. ደላሎች/የውጭ ምንዛሪ፣ የዋስትና፣ የክምችትና ሼር፣ የኢንሹራንስ ወኪሎች፣ የጉዞ አማካሪዎችና አቀነባባሪዎች፣ የሪል ኤስቴት፣ ግዢ፣ ሽያጭ፣ ኪራይ አቀነባባሪዎች (አስማሚዎች)፣ የቴክኒክ ዕቃዎች (መሣሪያዎች) ሽያጭ ተወካዮች፣ ኢንተርፕራይዞችንና ድርጅቶች በመወከል ዕቃና አገልግሎት ገዢዎች፣ በኢንሹራንስ የሚሸፈኑ የዕቃዎችና ንብረቶች ኪሳራ ገማቾች፣ አጫራቾች፣ በሌላ ቦታ ያልተገለፀ የፋይናንስና ሽያጭ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች፡፡

342. የንግድ ኤጀንቶችና ደላላዎች፣/ገዥና ሻጭ አገናኞች፣ ሽያጭና ግዢ አደራዳሪዎች/አስማሚዎች/ ሥራና ሠራተኛ አገናኞችና አዋዋዮች፣ ከጉምሩክ ጋር በመገናኘት ዕቃዎች ተገቢውን ፎርማሊቲ አሟልተው እንዲወጡ የማድረግ እንዲሁም የላኪነት/አስመጪነትና የመድህን ፈቃዶች መኖራቸው አረጋጋጮች (የመርከብ ላይ ደላሎች፣ያልተጠቀሱ የንግድና የዕቃ ደላሎች፣ የፎርማሊቲ አጣሪ ተወካዮች እዚህ ይጠቃለላሉ፡፡)

343. የአስተዳደርና የፍርድ ቤት ፀሐፊዎች፣ የሂሣብ መዝገብ ያዦች፣ የስታቲስቲክስ ማቲማቲክስና ተመሳሳይ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች፣ ኤክሲኪዩቲቭ ሴክሬታሪዎች፣ የማህበራዊ ጉዳይ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎችና የመሳሰሉት፣ እና በሌሎች ቦታ ያልተጠቀሱ የአስተዳደር መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች፣

344. የጉምሩክና የብሔራዊ ድንበር ተቆጣጣሪ ሠራተኞች፣ የቀረጥ ሥራ ሠራተኞች፣ የንግድ ፈቃድና የፓስፖርት ሠራተኞችና የመሳሰሉት ለምሳሌ፣ መለስተኛ ኢንስፐክተሮች፣ የዋጋና standard የመለኪያ ትክክለኛነት አጣሪ ኢንስፐክተሮች፣

345. ዘፋኞች፣ የመድረክ ተዋናዮችና ዲኮሬተሮች፣ የንግድ/የፋሽን ዲዛይነሮች አስተዋዋቂዎች የሬዲዮና የቴሌቪዥን አንባቢዎች፣ ስፖርተኞች የማስታወቂያና የፅሁፍ ሥራ የመሳሰሉት

346. የኃይማኖት መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች /ቄሶች፣ ሼኮች፣ ዲያቆናት ወንጌላውያን፣ መነኮሳት፣ ...

# ዋና ክፍል 4

# የጽህፈትና ተመሣሣይ ሠራተኞች

በዚ
ህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች ዋና ተግባራቶች የመረጃ ማደራጀት መመዝገብ፣የገቢና ወጪ ደብዳቤዎችን ብዛት ማስላት መለየት ሲሆን ዕውቀትና ልምድን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ዋንኛዎቹ ሥራዎችም የጽህፈት፣ የታይፒስትነት፣ የመረጃ መመዝገብና የማስላት ከደንበኞች ጋር በአብዛኛው ገንዘብ ነክና ቀጠሮ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ከማስተናገድ ጋር የተያያዙ የሥራ ዓይነቶች ናቸው፡፡ በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች በአብዛኛው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሙያ ማሰልጠኛ ተቋም የሙያ ሥልጠና ወይንም ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት ደረጃ ባላቸው የሚከናወኑ ናቸው፡፡

## 41. የቢሮ የጽህፈት ሠራተኞች

411.
ታይ

ፒስቶች፣ በኮምፒዩተር መረጃ ፀሐፊዎችና የመሳሰሉት

412. የሂሣብ መዝገብ ያዦች፣ የሂሣብ ፀሐፊዎች፣ የስታቲስቲክስና የፋይናንስ ፀሐፊዎችና ለምሳሌ፡- የስታትስቲክስ መረጃ ሰብሳቢዎች፣

413. የዕቃዎች ክምችትና የምርት ፀሐፊዎች፣ የአየር የየብስና የባቡር ትራንስፖርት ፀሐፊዎች የመንገድ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎችና የመሳሰሉት

414. የቤተ መጻሕፍት፣ የፖስታ፣ የፋይል ሥራ ፀሐፊዎች፣ ማመልከቻ ፀሐፊዎችና ሌሎች የቢሮ ጽህፈት ሠራተኞች

## 42. ደንበኞችን የማስተናገድ የጽህፈት ሥራ ሠራተኞች

421. ገንዘብ ተቀባዮችና ከፋዮች፣ ትኬት ቆራጮች (ከትራንስፖርት የተለየ ነው)፣ የፖስታ ቤት አስተናጋጆች፣ ገንዘብ ሰብሳቢዎች፣ ቆጣሪ አንባቢዎችና የመሳሰሉት

422. እንግዳ ተቀባዮች (የሆቴል፣ የሕክምናና የመሳሰሉት)፣ ቴሌፎን ኦፕሬተሮች ቲኬት ቆራጮች እና የመሳሰሉት

# ዋና ክፍል 5

# የአገልግሎት የሱቅና የገበያ ሽያጭ ሠራተኞች

በዚ
ህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች አብዛኛዎቹ ተግባራቶች ለግለሰቦች አገልግሎት የመስጠትን፣ የመከላከል አገልግሎት የመስጠትን፣ በሱቅና በገበያ ዕቃ የመሸጥ እውቀትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ዋና ክፍሉ በተለይም ከጉዞ፣ ከሆቴል፣ ከቡና ቤት አገልግሎቶች፣ ከግለሰብ እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ ከግለሰብና ከንብረት ጥበቃ አገልግሎቶች፣ የደንብ ስርዓት ማስከበር አገልግሎቶችና በሱቅና በገበያ የዕቃ ሽያጭ አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ አገልግሎት ሰጭዎችን ያጠቃልላል፡፡

## 51. ለግለሰብ አገልግሎት ሰጭዎችና የአደጋ/የወንጀል መከላከያ አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች

511. የጉዞ አስተናጋጆችና የመሳሰሉት (የአውሮፕላን፣ የባቡርና የመሳሰሉት አስተናጋጆች፣ አስጎብኝዎችና የመሳሰሉት)

512. የጠላ ቤት፣ የአረቄ ቤት፣የጠጅ ቤት፣ ሌሎች መጠጥ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ሻይ ቤቶች፣ ሬስቶራንቶች፣ ሆቴሎችና የመሳሰሉት አገልግሎት ሠራተኞችና ምግብ አብሳዮች (የጠላ ቤት፣አረቄ ቤቶች የቡና ቤት አስተናጋጆች፣ ወጥ ቤቶች፣ ባሬስታዎችና የመሳሰሉት)

513. ፀጉር ቆራጮች የውበት ሳሎን ሠራተኞች በሕፃናት ማሳደጊያዎች ተንከባካቢዎችና ሌሎች ለግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎችና የእነዚህ ሠራተኞች ተቆጣጣሪዎች

514. ፖሊሶች፣ የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች፣ የወንጀል ምርመራ የደህንነት ሠራተኞችና የመሳሰሉት

## 52. የሱቅና የጉልት ሽያጭ ሠራተኞችና ሞዴሎች

**521. የፋሽንና የሥነ ጥበብ ሞዴሎች**

522. የሱቅና የኪዮስክ አሻሻጮችና ቤንዚን ቀጂዎች (የጅምላና የችርቻሮ ንግድ በሚካሄድባቸው ሱቆች ውስጥ ዕቃ የሚሸጡ፣ የሚደረድሩና የሚያሻሽጡ)

523. በጉሊት፣ ሜዳ ላይ ባለ ገበያ እንዲሁም በመንገድ ላይ /ተቀምጠው/ ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ የሚሸጡ፣ የማገዶ እንጨት ነጋዴዎች

# ዋና ክፍል 6

# የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎችና ዓሣ አስጋሪዎች

በዚህ ክፍል የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው (ማለትም:- የማረስ፣ የመዝራት፣ የማረም፣ የመሰብሰብና የመሳሰሉት ተግባራት የሚከናወኑበትን ወቅትና ሁኔታ የሚያውቁ) አራሾች፣ የከብት ማርባት ዕውቀት ያላቸው ከብት አርቢዎች፣ የዓሣ ማጥመድ ሙያ ያላቸው ዓሣ አጥማጆች በዚህ ክፍል ይጠቃለላሉ:: በተጨማሪም በዚህ ክፍል ለንግድ ተግባር የሚያገለግሉ የሰብል፣ የከብት፣ የጥጥ፣ የሸንኮራ፣ የትምባሆ፣ ...ወዘተ ምርቶችን የሚያመርቱ በሥራው ላይ ተገቢው ዕውቀት ያላቸው ሠራተኞችን ያጠቃልላል:: በዚህ ክፍል የሚመደቡ ሠራተኞች የተለያዩ የዕውቀት ደረጃ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ::

## 61. ለንግድ በተቋቋሙ እርሻዎችና ድርጅቶች የሚሠሩ የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎች:-

611. የሰብል፣ ጥጥ፣ ሸንኮራ፣ ሻይ፣ ወይንና የመሳሰሉትን ለንግድ የሚያመርቱ ዕውቀቱ ያላቸው ገበሬዎች፣

612. የከብት፣ የዶሮና የመሳሰሉትን ለንግድ የሚያመርቱ ዕዉቀቱ ያላቸው ገበሬዎች

613. በደንና በከሰል ሥራ የተሠማሩ ዕውቀት ያላቸው ሠራተኞች

614. በዓሣ ማስገር በአደንና በመሳሰሉት የተሠማሩ ዕውቀቱ ያላቸው ሠራተኞች

## 62. በግልና በቤተሰብ እርሻ የተሠማሩ የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎችና ዓሣ አስጋሪዎች:-

621. በግልና በቤተሰብ እርሻ የተሰማሩ የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎች፣ ከብት አርቢዎችና ዓሣ አስጋሪዎች (የማሳ አዘገጃጀት፣ አስተራረስ፣ የሚዘራበትን ሠዓትና ለግብርና አስፈላጊ የሆነውን ዕውቀት ከወላጅ ወይም ከልምድ የቀሰሙና በሥራው የተሠማሩ ገበሬዎች፣ የከብት እርባታ እውቀት ያላቸው ከብት አርቢዎች የዓሣ ማጥመድ ሙያ ያላቸው ዓሣ አጥማጆች)

# ዋና ክፍል 7

# የዕደጥበብና ተመሳሳይ ሠራተኞች

በዚ
ህ ዋና ክፍል የሚመደቡት ሠራተኞች የዕደ ጥበብ ሙያ ያላቸውና ለዚህ ተግባር በጥቅም ላይ በሚውሉ መሣሪያዎች የመጠቀም ችሎታ ያላቸው የዕደ ጥበብ ምርቱን ለማምረት የሚያስፈልጉ ሥራዎችን ዓይነት በትክክል የሚረዱና የምርቱንም ጥቅም የተረዱ ሠራተኞች ናቸው:: በዚህ ክፍል የሚመደቡት ሠራተኞች በማዕድን ማውጣት፣ የሕንፃ ሥራ የተለያዩ የዕደ ጥበብ ውጤቶችን በማምረት ተግባር ላይ የተሠማሩ ናቸው::

## 71. የማዕድን አውጭዎችና የሕንፃ ሥራ ሠራተኞች

711. የማዕድን፣ የድንጋይ፣ የአሸዋና የመሳሰሉት አውጭዎችና የድንጋይ ጠራቢዎቸ (ዲማሚት አፈንጂዎች፣ የካባ ሠራተኞች በዚህ ክፍል ይጠቃለላሉ::)

712. ግንበኞች፣ አናፂዎች የመሳሰሉትና ባህላዊ ቤቶችን ፣ ጎጆዎችን ...ወዘተ ሠሪዎች:: (የእንጨት ጀልባና ታንኳ ሠሪዎች እዚህ ይጠቃለላሉ::)

713. ለሳኞች፣ የቧንቧ ሥራ ሠራተኞች፣ የጣሪያ ሥራ ሠራተኞች (የጣሪያ አዋቂዎች)፣ የመስታወት ሠራተኞች፣ የሕንፃ ኤሌክትሪሺያኖችና የመሳሰሉት የሕንፃና የፊኒሽንግ ወይም የማጠናቀቅ ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች

714. ቀለም ቀቢዎች (የሕንፃዎችና፣ ሌሎች በሌላ ቦታ ያልተገለፁ የተመረቱ ቁሳቁሶች ለምሳሌ የመኪና ቀለም መቀባትን ያጠቃልላል)

## 72. የብረት፣ የማሽኖችና ተመሳሳይ ሠራተኞች

721. ብረት በያጆች፣ ብረት አቅላጮች፣ የጠፍጣፋ ብረት ሠራተኞች፣ የመሠረትና የምሶሶ የሚሆን ፌሮ ብረት አዘጋጆችና ብረት ወጣሪዎች፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ የዕደጥበብ ሠራተኞችና

722. ቀጥቃጮች፣ የብረታ ብረት የዕደጥበብ ምርት አምራቾችና የመሳሰሉት

723. የመኪና ሜካኒኮች፣ የአውሮፕላን ኢንጂን ሜካኒኮችና ገጣሚዎች፣ ጎሚስታዎች፣ ላቫጆ (የዘይትና ግሪሲንግ የሚያደርጉ)ና ሌሎች ተመሳሳይ ሠራተኞች::

724. የኤሌክትሪካልና የኤሌክትሮኒክስ ሚካኒኮች፣ የቴሌፎን መሥመር ዘርጊዎች፣ ጠጋኞችና ኬብል አገናኞች፣ የጋራዥ ኤሌክትሪሸያንና የመሳሰሉት:: (የሬድዮ፣ ቴሌቪዥንንና የመሳሰሉት አዳሾች እዚህ ይጠቃለላሉ::)

## 73. አንጥረኞች፣ የሸክላ ሠራተኞች፣ የእንጨትና የቆዳ ዕደጥበብ ሠራተኞችና የኀትመት ሠራተኞች:- (የዕደጥበብ ውጤቶች)

731. አንጥረኞች፣ ወርቅ፣ ሠዓትና ተመሳሳይ የሆኑ ጥንቃቄ የሚፈልጉ መሣሪያዎች ሠሪዎችና ጠጋኞች (የሙዚቃ መሳሪያ ሠሪዎች እዚህ ይጠቃለላሉ::)

732. ሸክላ፣ መስታወት፣ ሠሪዎችና የሸክላ መስታወትና ሲራሚክስ ምርቶችን ቀለም ቀቢዎችና ተመሳሳይ ሠራተኞች::

733. የእንጨት፣ የቀርከሃ፣ የቃጫ፣ የጨርቅና የቆዳ ቁሳቁሶች የዕደጥበብ ውጤቶች ሰሪዎች

734. የቀላል የኅትመት ሥራ ሰሪዎች፣ ፎቶግራፍ አንሺዎችና የፊልም አጣቢዎች፣ የመጽሐፍ ጠራዦችና የመሳሰሉት (አታሚዎች፣ ፊደል ለቃሚዎች፣ ስቴሪዮና ኤሌክትሮ ታይፐሮች፣ ብረት ላይ አታሚዎች፣ ጨርቃጨርቅ ላይ አታሚዎች እና የመሳሰሉት እዚህ ይጠቃለላሉ)

**74. ሌሎች የዕደጥበብና ተመሳሳይ ሥራዎች:-**

741. ጠላ ጠማቂዎች፣ አረቄ አውጪዎች፣ እንጀራና ዳቦ ጋጋሪዎች፣ የኬክና ሌሎች ጣፋጭ ምግብ ዝግጅት ሠራተኞች፣ የልኳንዳ ሠራተኞች ቅቤና ዓይብ አውጭዎች፣ የትምባሆ አዘጋጆች፣ በርበሬ ለቅማ የምትሸጥና የመሳሰሉት፣ የምግብና መጠጥ ቀማሾችና ደረጃ ሠጪዎች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች ሳይበላሹ ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ አድራጊዎችና ምግብ አዘጋጆች የመሳሰሉት::

742. ሰሌንና ዘንቢል ሠሪዎች፣ ቁምሳጥኖችን ቡፌሾችንና ሌሎች የእንጨት ቁሳቁሶችን የሚያመርቱ፣ ኪስ ወረቀት የሚሠሩ፣

743. ሸማኔዎች፣ ፈታዮች፣ ልብስ ሠፊዎች ሥጋጃ ሠሪዎች ፍራሽ አዳሽ፣ ሶፋ አዳሽ፣ ታፒሰሪና የመሳሰሉት

744. ፋቂዎች፣ ጫማ ሠፊዎች፣ ጫማ ጠጋኝና የመሳሰሉት

# ዋና ክፍል 8

# የማምረቻ መሣሪያዎች ኦፕሬተሮችና ገጣጣሚዎች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ ሠራተኞች በአብዛኛው ትላልቅ ማሽነሪዎችን የማንቀሳቀስና የመጠቀም (ኦፕሬት የማድረግ) ዕውቀት ያላቸው ናቸው:: አብዛኛዎቹም የሥራ ዓይነቶች ማዕድን አውጭዎች የማምረቻ መሣሪያዎች ኦፕሬተሮች፣ ሾፌሮች ናቸው::

**81. በቋሚነት የተተከሉ መሣሪያዎችና የመሳሰሉት ኦፕሬተሮች**

811. የማዕድን ማውጫና ማጣሪያ ማሽኖች ኦፕሬተሮች

812. የብረት ማቅለጫና ተመሳሳይ ማሽኖች ኦፕሬተሮች

813. የመስታወት፣ የሴራሚክስና ተመሣሣይ ማሽነሪዎች ኦፕሬተሮች

814. የእንጨት መሰንጠቂያና የወረቀት ማምረቻ ማሽነሪዎች ኦፕሬተሮች

815. የኬሚካል፣ የፔትሮሊየምና የተፈጥሮ ጋዝ ማሽኖች ኦፕሬተሮች

816. የኤሌክትሪክና ሌሎች የኃይል ማመንጫ መሳሪያዎች ኦፕሬተሮች

817. የመገጣጠሚያ ማሽነሪ ኦፕሬተሮች

**82. ማሽን ኦፕሬተሮችና ገጣጣሚዎች**

821. የሲሚንቶ፣ የብረት ቅርፅ ማውጣትና የመሳሰሉት የማዕድንና ከማዕድናት ከሚገኙ ንጥረ ነገሮች ጋር የተያያዙ ማሽኖችን ኦፕሬተሮች

822. የኬሚካል፣ ፋርማሲቲካል፣ የመፈንዳት ፀባይ ያላቸው (ፈንጂዎች) እና ሌሎች ከተመሳሳይ የኬሚካል ውጤቶች ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፕሬተሮች (የክብሪት ማምረቻ ማሽነሪ ኦፕሬተሮች፣ የፊልምና ፎቶግራፍ ማሳደጊያ ማሽነሪ ኦፕሬተሮች)

823.

ከላስ

ቲክና ከጎማ ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፐሬተሮች

824.

የእን

ጨት ውጤቶች እና ከእንጨት ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፐሬተሮች

825.

ከጎ

ትመት፣ ከመሰበድና ከወረቀት ውጤቶች ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፐሬተሮች

826. ከድርና ማግ ከጨርቃጨርቅ ምርትና ስፌት፣ ከቆዳና ከጫማ ጋር የተያያዙ ማሽን ኦፐሬተሮች፣ የማቅለምና የላውንደሪ ማሽን ኦፐሬተሮች

827. ከምግብ (ሥጋ፣ ወተት፣ ሰብል፣ ከረሜላ፣ ስኳር፣ ሻይ፣ ቡና፣ ቢራ፣ ለስላሳ፣ ... ወዘተ) ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፐሬተሮች ፣ ወፍጮ ቤት ሠራተኛ

828. ተገጣጥመው የሚሠሩ መኪኖች፣ አውሮፕላኖችን፣ የኤሌክትሪካልና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን ከብረት፣ ከፕላስቲክ፣ ከጎማ፣ ከቆዳ ከእንጨት ወይም ከሌሎች ዕቃዎችን የሚሰሩ ዕቃዎች ገጣጣሚዎች

## 83. ሾፌሮችና ተንቀሳቃሽ ማሽን ኦፐሬተሮች

831. የባቡርና ተመሳሳይ መጓሪያዎች ነጂዎችና ኦፐሬተሮች

832. የመኪና፣ የታክሲ፣ የአውቶብስ፣ የሞተር ብስክሌት፣ የጭነት መኪኖች ነጂዎች

833. የክሬኖች፣ የዕቃ ማንሻ ተንቀሳቃሽ ማሽን ኦፐሬተሮች፣ ትራክተሮችና ሌሎች ከግብርና ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፐሬተሮች

834. የመርከብ ላይ ሠራተኞችና ተመሳሳዮች

# ዋና ክፍል 9

# ዝቅተኛ ሥራ ሠራተኞች

በዚ

ህ ዋና ክፍል የሚመደቡ ሠራተኞች ዝቅተኛ የሆኑ ሥራዎችን የማካሄድ እውቀት ያላቸው ናቸው። በአብዛኛው ውም በእጅ የሚያዙ መሣሪያዎች በስተቀር የተለየ መሣሪያ የማይጠቀሙ ሲሆን ሥራቸውም በአብዛኛው የጉልበትን በመጠቀም የሚከናወን ነው። በሥራው ላይም ውሳኔ የመስጠታቸው እድል አነስተኛ ነው። አብዛኞቹ በዚህ ክፍል የሚመደቡ ሥራዎች በየመንገዱ የሽያጭ ተግባር የሚያከናውኑ፣ ዘበኝነት፣ የቤት ሠራተኝነት፣ የማዕድን ቁፈራ ወዛደሮች፣ የግብርናና የከብት እርባታ ዝቅተኛ ሠራተኞች፣ የማዕድን ማውጣት የኮንስትራክሽንና የማምረቻ ፋብሪካዎች ተራ ወዛደሮች ናቸው።

## 91. ዝቅተኛ የሽያጭና የአገልግሎት ሥራ ሠራተኞች

911. ቆሎ አዟሪዎች፣ የልዋጭ ነጋዴዎች፣ ዕቃ በየቤቱ እያዞሩ የሚሸጡ፣ በየመንገዱ እየዞሩ ዕቃ የሚሸጡ፣ ጋዜጣ አዟሪዎችና የመሳሰሉት ዕቃ ሻጮች

912. ሊስትሮዎች፣ በየመንገዱ መኪና የሚያጥቡና የመሳሰሉት በመንገድ አገልግሎት የሚሰጡ

913. የቤት ሠራተኞች፣ ልብስ አጣቢዎች፣ ሹሩባ ሠሪዎች የቡና ቤት ጽዳት ሠራተኞች፣ የቡና ቤት ሣህን አጣቢዎች፣ የቡና ቤት አልጋ አንጣፊዎችና ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ

914. ዘበኞች /የግለሰብ ቤትንም ይጨምራል/፣ ዕቃ ተሸካሚዎች፣ ተላላኪዎች፣ የቢሮ ጽዳት ሠራተኞች፣ መንገድ ጠራጊዎች፣ ቆሻሻ ሰብሳቢዎች፣ በግቢ ውስጥ መኪና አጣቢዎችና ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ

## 92. ዝቅተኛ የግብርናና የዓሣ ማስገር ሠራተኞች

921. እረኞች፣ ዝቅተኛ የእርሻ ሥራ፣ የዓሣ ማስገርና የደን ሥራ ሠራተኞች (የሥራው ዓይነት የተለየ ዕውቀት የማይጠይቅ ሆኖ ከሌሎች በሥራው ላይ ዕውቀት ካላቸው ገበሬዎች ጋር በረዳትነት ወይም በአጋዥነት የግብርና ሥራ የሚያካሂዱ ሠራተኞች)

## 93. የማዕድን ቁፋሮ፣ የሕንፃ ሥራ፣ የማምረቻና የትራንስፖርት ሥራ የቀን ሠራተኞችና ወዛደሮች

931. የማዕድን ቁፋሮ፣ የድንጋይ ማውጣት፣ የኮንስትራክሽንና የጥገና ሥራ ወዛደሮች፣

932. የማምረቻ ፋብሪካዎች ተራ ወዛደሮችና የፋብሪካ ቡና ለቃሚዎች

933. በእጅ ወይም በፔዳል የሚንቀሳቀሱ፣ በእንስሳት የሚጎተቱ /እንደ.ጋሪ/ ተንቀሳቃሾችና መዣሪያዎች ነጅዎች፣ ጭነትና ሌሎች ዓዞችን የሚያስተናግዱ ወዛደሮች /አውታንቲዎች፣ ወያላዎችና የመሳሰሉት በዚህ ይጠቃለላሉ/ ዕቃ ጫኝና አውራጆች፣ በጋማ ከብት ዕቃ የሚያጓጉዙ

# ዋና ክፍል 0

## የጦር ኃይል አባላት

## 01.

የጦ
ር ኃይል አባላት (ሲቪሎችን አይጨምርም)

011. የጦር ኃይል አባላት

# የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት /የኢንዱስትሪ/ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች/ ምደባና መለያ ኮድ ዝርዝር

## መግቢያ

የኢ
ንዱስትሪ ምደባ ዋና ዓላማ ድርጅቶችን በየእንቅስቃሴአቸው ዓይነት ለመመደብ ሲሆን ትክክለኛ የሆነ የኢንዱስትሪ ምደባም የአንድን አገር ኢኮኖሚ አቋምና ዝንባሌ ለመገምገም ይረዳል::

በአ
ንድ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የተሰማራ ግለሰብ የኢንዱስትሪ ምደባ የሚካሄደው ግለሰቡ በተሰማራበት ድርጅት የመጫረሻ /final/ ዋና ምርት ወይም አገልግሎት መሠረት ነው::

በጥ
ናቱ መጠይቅ ላይ በዓምድ 32 የግለሰቦች የኢንዱስትሪ መደብ ማለትም የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ተፅፎ ይገኛል:: የዚህንም ምድብ ኮድ ከተሰጠው የኢንዱስትሪ ኮድ ዝርዝር በመምሪጥ በ1996 የከተሞች የስራ ስምሪት ጥናት መጠይቅ በዓምድ 32 በተዘጋጁት ካርድ ኮለሞች ይሞላል::

ለም
ሳሌ በአንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በገንዘብ ያዥነት የሚሠራ ግለሰብ

የኢንዱስትሪ ምደባ እንደሚከተለው ይሆናል:: ድርጅቱ ማለትም ትምህርት ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት አገልግሎት ሲሆን ይኸውም በመጠይቁ በዓምድ 36 ተፅፎ እናገኘዋለን:: ለዚህም ተገቢው ኮድ በተሰጡት ሦሥት ካርድ ኮለሞች ከገጽ 21 ከዋና ክፍል አስራ ሁለት ከንዑስ ክፍል 80 ተመርጦ ለዚህ ኢንዱስትሪ ዓይነት ተስማሚው ኮድ 802 ስለሆነ ይኸው ኮድ ይሞላል::

የሌ
ላ ግለሰብ የኢንዱስትሪ ዓይነት በዓምድ 32 ጠላ አምርቶ መቸርቸር የሚል ተሞልቶ ከሆነ ጠላውን ጠምቀው በችርቻሮ ለሚሸጡ የኢንዱስትሪ ዓይነት ከኢንዱስትሪ ኮድ ምደባ በገጽ 22 ከዋና ክፍል ስድስት ከንዑስ ክፍል 55 ኮድ 552 ስለሆነ ይኸው ተመርጦ በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል:: ነገር ግን ጠላውን በጅምላ ገዝተው በጅምላ የሚሸጡ ከሆነ የግለሰቡ ኢንዱስትሪ በጅምላ ንግድ በመመደብ በካርድ ኮለሞቹ ኮድ 512 ይሞላላቸዋል::

በዓ
ምድ 32 የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምንድን ነው የሚለው ጥያቄ እድሜአቸው አስር ዓመትና በላይ ለሆኑ ግለሰቦች በሙሉ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው:: ነገር ግን ዕድሜአቸው አስር ዓመትና በላይ ሆኖ በዓምዱ የኢንዱስትሪ ዓይነት ያልተሞላላቸው ግለሰቦች ቢገኙ መረጃው መሞላት ሲገባው ያልተሞላ መሆኑን ለማመልከት ኮድ 999 በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል::

# የኢንዱስትሪ ወይም የድርጅት ምርት፣ ንግድ ወይም አገልግሎት

## ምደባ መለያ ኮድ ዝርዝር

## ዋና ክፍል - አንድ

## ግብርና፣ አደን፣ ደን ሀብትና አሣ ማስገር

**01.**

ግብ
ርና፣ አደንና ተመሣሣይ ምርቶችና አገልግሎቶች

**011.** ቋሚና ጊዜያዊ ሰብሎች የእርሻ ምርት፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች፣ ፍራፍሬ፣ አትክልትና ለገበያ የሚቀርቡ ሰብሎችን ማምረት /ጤፍ፣ ስንዴ፣ ...፣ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ መንደሪን፣ ...፣ ድንች፣ ሸንኮርት፣ ለውዝ፣ ቡና ...ወዘተ/ እንዲሁም የተለያዩ የዘር እህሎችን ማምረትና የአትክልት ችግኞችን ማፍላት እና ሌሎች በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ሰብሎችን ማምረት በዚህ ይጠቃለላሉ::

**012.** ከብት እርባታ /ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ፈረስ፣ ... ወዘተ ማርባት፣ የዶሮና ንብ እርባታ፣ ወተት፣ የሌሎች እንስሳት እርባታና በሌላ ቦታ ያልተገለፁ የእንስሳት ተዋፅዖዎችን (ምሳሌ ፀጉር ...ወዘተ) በእንስሳት አርቢው ማምረት፣ ...ወዘተ/

**013.**
እርሻና ከብት እርባታ /ጥምር ግብርና/ (ሰብሎችን ማምረት ከእንስሳት እርባታ ጋር)

**014.** የግብርናና ከብት እርባታ አገልግሎት መስጠት የእንስሳት ሕክምናን ሳይጨምር /ፀረ-ሰብልና ፀረ-እንስሳት የሆኑ ተባዮችንና በሽታዎችን መከላከል፣ የእርሻ መሳሪያዎችን ትራክተር፣ ኮምባይነርና የመሣሠሉ ማከራየት (ከኦፕሬተር ጋር)፣ የመስኖ ሥራ፣ ከብቶችን ማዳቀል ሥራ ...ወዘተ/ እንዲሁም ሰብልን ለገበያ ለማቅረብ የማጠብ፣የማድረቅ፣የመፈልፈል... ወዘተ. አገልግሎት መስጠት፣

**015.** አደን /ለምግብ፣ ለሽያጭ፣ ለምርምር፣ ስጋቸው ፣ ቆዳቸውን ወይም ፀጉራቸውን ለመጠቀም ወይም ለማራባት የአደን ሥራ ወይም ልማት ማካሄድ/

**02.** የደን ሀብት ምርት ማምረት

020. የደን ሀብት ምርት ማምረት /ደን ማልማት፣ መንከባከብና ጥቅም ላይ ማዋል/ በተፈጥሮና በሰው የሚለሙ ዛፎችን ለማገዶና ለተለያዩ ጥቅሞች እንዲውሉ ማዘጋጀት ለምሳሌ ከሰል ማክሰል፣ ጣውላ ማዘጋጀት ...ወዘተ

**05. ዓሣ ማስገር**

050. ዓሣ ማስገርና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ከባህር፣ ከሐይቆች፣ ከውቅያኖሶች፣ ...ወዘተ ማምረት፣ ከዓሣ ማምረት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሌሎች የዓሣ ማስገር ሥራዎች አገልግሎቶችን መስጠት

## ዋና ክፍል ሁለት

## ማዕድን ድንጋይና አሸዋ ማውጣት

**10. የድንጋይ ከሰልና የሊግናይት ፒት ማምረት**

101. የድንጋይ ከሰል፣ ሊግናይት ፒት ማምረት

**11. ያልተጣራ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ ማምረት፣ ዘይትና ጋዝ ለመፈለግ የሚደረጉና ተመሳሳይ አገልግሎቶች /ነገር ግን የቅየሳ ሥራን አይጨምርም/**

111. ያልተጣራ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ ማምረት፣ ዘይትና ጋዝ ለመፈለግ የሚደረጉና ተመሳሳይ አገልግሎቶች /ነገር ግን የቅየሳን ሥራን አይጨምርም/

**12. የወርቅ የብረትና የመሳሰሉት ማዕድናትን ማምረት**

120. የወርቅ የመዳብ እንዲሁም ብረት ነክ የመሳሰሉት ማዕድናትን ማምረት

**13. ሌሎች ማዕድን፣ ድንጋይና አሸዋ ማውጣት**

131. ድንጋይ፣ አሸዋና ሸክላ ማውጣት (ማምረት)

132. ከዚህ በላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ማዕድናትን ማውጣት /ኬሚካሎች፣ የማዳበሪያ ማዕድናት ጨው፣ ...ወዘተ ማውጣት/

## ዋና ክፍል- ሦሥት

## ማኒፋክቸሪንግ

ማኒፋክቸሪንግ አንድን ዕቃ ወደ ሌላ አዲስ ዓይነት ዕቃ ወይም ምርት የመለወጥ ተግባር ነው። የመለወጡ ተግባር ዘመናዊ የሞተር ማሽኖችን ወይም በእጅ በመጠቀም በፋብሪካ ወይም በመኖሪያ ቤት ውስጥ ...ወዘተ ሊከናወን ይችላል። በተጨማሪም የተለያዩ ምርቶችን መገጣጠም ወይም የተለያዩ ማሽኖችንና መሣሪያዎችን በንግድ፣ በማዕድንና ሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ገጣጥሞ መትከል እንደ ማምረት ተቆጥሮ የተተከሉት የማሽን ዓይነቶች በሚመደቡበት የማምረት መለያ ኮድ ዉስጥ ይመደባሉ። የተለያዩ የፋብሪካና የንግድ ማሽኖችንና መሳሪያዎችን በዋነኝነት የመጠገን ሥራ እንደ ማምረት ተቆጥሮ ማሽኖቹና መሣሪያዎቹ በሚመደቡበት የማምረት መለያ ኮድ ውስጥ ይመደባሉ። ቀደም ሲል የተመረቱ ምርቶችን በከፍተኛ ደረጃ መለወጥ ወይም እንደገና መስራት እንደ ማምረት ይቆጠራል።

**15. የምግብ ውጤቶችን ማምረት**

151. የከብት፣ የበግ፣ የዶሮና የመሳሰሉ እንስሳትን ማረድ፣ ሥጋውን ማዘጋጀትና እንዳይበላሽ መጠበቅ /ቄራዎች፣ በቆርቆሮ ወይም በሌላ ዕቃ ሥጋ ማሸግና ማዘጋጀት የመሳሰሉት/

152. ከባሕር፣ ከሐይቆችና ከወንዞች የሚገኙ እንደ ዓሣ የመሳሰሉትን በቆርቆሮ ወይም በሌላ ዕቃ ማሸግ፣ እንዳይበላሹ መጠበቅና ማዘጋጀት

153. ትኩስ፣ ደረቅ ወይም በማቀዝቀዣ የተጠበቀ አትክልትና ፍራፍሬ በቆርቆሮ ወይም በሌላ ማሸግና ማዘጋጀት /በቆርቆሮ የታሸጉ የአትክልትና ፍራፍሬ ጭማቂዎችን ማዘጋጀት ይጨምራል/

154. ከቅባት እህሎች፣ ከአትክልትና ከእንስሳት ዘይትና ስብ (ፋትስ) ማምረት /የዘይት መጭመቂያዎች እዚህ ይመደባሉ/

155. ወተትና የወተት ተዋፅዖ ማዘጋጀት /ቅቤ፣ ቺዝ፣ ማሸግ ...ወዘተ ማዘጋጀት ነገር ግን ወተት በማለብ ለቤታቸው የሚያዘጋጁ በኮድ 012 ወይም 013 ይመደባሉ/

156. እህል በወፍጮ ፈጭቶ ማዘጋጀት /እህል ገዝተው በመፍጨት ለመንግሥት፣ ለነጋዴዎች፣ ለግለሰቦች ወይም ለሌላ ድርጅት የሚያቀርቡ ፋብሪካዎች ወይም ወፍጮ ቤቶች በዚህ ይመደባሉ:: ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያ ምግብ ማደራጃና ሆለታ ዱቄት ፋብሪካ የመሳሰሉት፣ ነገር ግን ከግለሰቦች፣ ከቤተሰቦች ወይም ከነጋዴዎች እህል ቀርቦላቸው የአገልግሎት ዋጋ እያስከፈሉ የሚፈጩ በአገልግሎት ዘርፍ ይመደባሉ/፣ ከእህል የእንስሳት መኖ ማዘጋጀት/

157. የጋገራ ውጤቶች ማምረት /እንጀራ፣ ዳቦ፣ ኬክና ብስኩት፣...ወዘተ ማምረት/

158. ስኳርና ከረሜላዎችን ማምረት /ወንጂ ስኳር ፋብሪካ፣ ገነት ከረሜላ ፋብሪካ፣ሸንኮራ ...ወዘተ/

159. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች የምግብ ዓይነቶች ማምረት/ ማኮረኒ፣ ፓስታ፣ ቡና መቁላት፣ መፍጨትና ማሸግ፣ ቅመማቅመምን ፈጭቶና አሽጎ ማዘጋጀት፣ እርሾ ...ወዘተ/

## 16. ትምባሆና መጠጦችን ማምረት

161. የአልኮል መጠጦች ማምረት /ሞላ ማሩና መርከበኛ የመጠጥ ፋብሪካ የመሳሰሉት/

162. ወይን ጠጅ ማምረት /ከሰምና የመሳሰሉ የወይን ፋብሪካዎች/

163. ቢራ ማምረት /ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ በደሌ፣ ...ወዘተ ቢራ ፋብሪካዎች/

164. ለስላሳ መጠጥ ወይም ሚኒራል ውሃ /የአምቦ ውሃ የመሳሰሉ/ ማምረት

165. ጠላ፣ ቦርዴና የመሳሰሉትን መጥመቅ /በጠማቂው ድርጅት ጠላ በችርቻሮ ከተሸጠ ድርጅቱ በንግድ ዘርፍ ይመደባል፣ ነገር ግን ጠማቂው ድርጅት ጠላውን ለሌላ ነጋዴ ወይም ድርጅት በጅምላ ቢሸጥ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ/

166. ጠጅ መጥመቅ /ከላይ ለጠላ ጠማቂ ድርጅት የተሰጠው ማሳሰቢያ ጠጅንም በሚመለከት ያገለግላል/

167. ካቲካላ መጥመቅ /ከላይ ለጠላ ጠማቂ ድርጅት የተሰጠው ማሳሰቢያ ካቲካላንም በሚመለከት ያገለግላል/

168. የትምባሆ ውጤቶች የሆኑ ሲጋራዎች፣ ሲጋሮች፣ ...ወዘተ ማምረት /የትምባሆ ማብቀልና ቅጠሎችን ማዘጋጀት በግብርና ውስጥ ይመደባሉ/

169. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች መጠጥና ትምባሆ ማምረት

## 17. ጨርቃ ጨርቅ ማምረት

171. መፈልቀቅ፣ ማዳወር፣ መፍተል፣ ማቅለምና ማጠናቀቅ /አደይ አበባ ጥጥ ፋብሪካ፣ የኢትዮጵያ ክር ፋብሪካና በሽመና የአገር ባሕል ልብሶች ማምረት/

172. ከሚለበሱ ልብሶች በስተቀር ከጨርቃ ጨርቅ እንደ መጋረጃ፣ የአልጋ ልብስ፣ አንሶላ፣ የትራስ ልብስ፣ የመኪና መቀመጫ ልባሶች፣ ድንኳኖች፣ የመኝታ ከረጢት፣ ባንዲራ፣ የቆሻሻ መወልወያ፣ የወለል ምንጣፎች፣ መረብ፣ ገመድ፣ ያልተለፋ ቆዳ ...ወዘተ ማምረትና እንዲሁም በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን ማምረት

173. አሠራራቸው አንድ ወጥ ሆኖ ሳይገጣጠሙ በቀጥታ ሊለበሱ የሚችሉ በእጅ ወይም በማሽን የሚሰሩ ጥልፎችና ልብሶች ለምሳሌ ስቶኪንጎች፣ ካልሲዎች፣ ሹራቦች፣ ...ወዘተ ማምረት

## 18. የሚለበሱ ልብሶችን ማምረት፣ ከፀጉር የሚሰሩ ልብሶችን ማቅለምና ማዘጋጀት

181. ከፀጉር ከሚሠሩ ልብሶች በስተቀር የሚለበሱ የጨርቅ ልብሶችን ማምረት /በዚህ ኮድ የሚጠቃለሉ በአጠቃላይ ጨርቁ ተቀዶና ተገጣጥሞ የሚዘጋጅ ሲሆን ነው፡፡ በተጨማሪ ጨርቁን ገዝተውና ሰፍተው ወይም አጠናቀው ለሽያጭ የሚያቀርቡ፣ ጨርቅ ቀርቦላቸው የአገልግሎት ዋጋ እያስከፈሉ ልብስ የሚሰፉ ሁሉ በዚህ ክፍል ይመደባሉ፡፡ የልብሶቹም ዓይነት የወንዶች፣ የሴቶችና የልጆች ሆኖ የውጭ ወይም የውስጥ ልብሶች፣ የሥራ ወይም የስፖርት ልብሶች፣ ኮፍያዎች፣ ቀበቶዎች፣ ከቆዳ የተሠሩ ልብሶች ...ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡/ ነገር ግን አሠራራቸው አንድ ወጥ ሆኖ ሳይገጣጠሙ በቀጥታ ሊለበሱ የሚችሉ በእጅ ወይም በማሽን የሚሰሩ ጥልፎችና ልብሶች ለምሳሌ ስቶኪንጎች፣ ካልሲዎች፣ ...ወዘተ በኮድ 173 ሥር እንጂ በዚህ አይካተቱም፡፡

182. ከእንስሳት ፀጉርማ ቆዳ የሚሠሩ ልብሶችን ማቅለምና ማዘጋጀት፣ እስከ ፀጉራቸው ካሉ ቆዳዎች ወይም ሌጦዎች ዕቃዎችን ማምረት

## 19. ቆዳ ማልፋት፣ ማለስለስና ማዘጋጀት፣ በፋብሪካ ወይም በቤት ውስጥ ቆዳ ማዘጋጀት የቆዳ ሻንጣዎች፣ የእጅ ቦርሳዎች፣ ኮርቻዎች፣ የተለያዩ የፈረስ ጌጣጌጦችና ጫማዎች ማምረት

191. ቆዳ ማልፋት፣ ማለስለስና ማዘጋጀት /በፋብሪካ ወይም በቤት ውስጥ ቆዳ ማዘጋጀት ለምሳሌ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ/፣ የቆዳ ሻንጣዎች፣ የእጅ ቦርሳዎች፣ ኮርቻና የኮርቻ ዕቃዎች ማምረት በተጨማሪም የሚለበሱ የቆዳ ልብሶችን ማምረት በዚህ ይከተታሉ

192. ከጨርቅ በስተቀር ከሌሎች ማቴሪያሎች ጫማዎችን ማምረት፣ በተጫማሪም የጫማ ሶሎችንና ሌሎች የጫማ ክፍሎችን ማምረት

## 20. ከቤትና ከቢሮ ዕቃዎች በስተቀር እንጨትና የእንጨት ውጤቶችንና ቡሽ ማምረት

201. እንጨት መሰንጠቅና ማዘጋጀት /ትላልቅና ትናንሽ የእንጨት መሰንጠቂያና ማዘጋጃ ድርጅቶች/

202. ከቤትና ከቢሮ ዕቃዎች በስተቀር የእንጨት፣ የቀርከሃና የሸምበቆ ውጤቶችን ማምረት /የአናፂ መሣሪያዎች፣ ሳጥኖች፣ በርሚሎች፣ የተለያዩ በእንጨት የተሰሩ የእጅ መሣሪያዎች፣ በእንጨት የተሰሩ የወጥ ቤት ዕቃዎች፣ ...ወዘተ/

## 21.

የወ

ረቀትና የወረቀት ውጤቶችን ማምረት

210. ወረቀት፣ የወረቀት ውጤቶች (ለምሳሌ ሶፍት) የወረቀት ቦርድ /ክርታስና የመሳሰሉ የወረቀት ዕቃዎች/ ማምረት፣

## 22. ማተም፣ መጠረዝና ማባዛት

221. ማተም /የተዘጋጁ መጻህፍት፣ ጋዜጣዎች፣ ጆርናሎች፣ መጽሔቶች፣ ...ወዘተ ጽሁፎችን መጠረዝና ማተም፣ ማባዛትና ፎቶ ኮፒ ሥራዎችንም ያጠቃልላል/

222. የተቀረጹ ሪኮርዶችን ማባዛት /ካሴቶች፣ ቪዲዮ ቴፖች፣ የኮምፒዩተር ዲስኮችን ከኦሪጅናል ኮፒዎች ላይ ማባዛት፣ ነገር ግን ኦሪጅናል የቪዲዮ ቴፖችና ተንቀሳቃሽ ፊልሞችን ማተም ወይም መቅረጽ በዚህ አይጠቃለሉም/

## 23. የተጣራ የነዳጅ ውጤቶችን ማምረት

231. የተጣራ የነዳጅ ውጤቶችን ማምረት

## 24. ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶችን ማምረት

241. ከማዳበሪያ በስተቀር መሠረታዊ የኢንዱስትሪ ኬሚካል ማምረት /የኢንዱስትሪ ጋዝ የመሳሰሉ ማምረት/

242. ማዳበሪያ የናይትሮጅን ኮምፓውንድ ማምረት

243. ፕላስቲክና ፕላስቲክ መሰል ጎማዎችን በቀዳሚነት ማምረት

244. ፀረ-ተባይና ሌሎች የግብርና ኬሚካል ውጤቶችን ማምረት

245. ቀለም፣ ቫርኒሽና የመሳሰሉትን የማቅለሚያ፣ የማተሚያ ቀለሞችንና ማስተሾችን ማምረት

246. የተለያዩ መድሃኒቶችና የመድሃኒት ኬሚካሎች ማምረት /የኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካና የሀገር ባህል መድሃኒት አምራቾች የመሳሰሉ/

247. ሳሙና፣ ሽቶና የንጽህና መጠበቂያ ዕቃዎች እንደ ጥርስ ሳሙና፣ ኒቪያ ክሬም፣ የተለያዩ ሳሙናና ሰንደል የመሳሰሉ ማምረት የጫማ ቀለሞችን፣ ማስቲሾችን፣ ለወለልና ለመሳሰሉት ሰም ማምረት ያካትታል፣

248. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶችን ማምረት /ፈንጂዎች፣ የተለያዩ የቅባት ዘይቶች፣ የመጻፊያ ቀለሞች፣ ...ወዘተ/ ሰው ሰራሽ ክር ማምረት

## 25. የጎማና ፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት

251. ጎማና ከመነዳሪያ ማምረት /አዲስ ጎማ ፋብሪካና የጎማ ቁጠባ የመሳሰሉ/እንዲሁም በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የጐማ ውጤቶችን ማምረት፣ ነገር ግን የሚከራይ በረባሶ በኮድ 192 ይካተታል።

252. የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት /እንደ ኢትዮ ፕላስቲከ ፋብሪካ የመሳሰሉና ከፕላስቲክ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለምሳሌ ለወለል ምንጣፍ የሚሆን፣ ለመፀዳጃ ቤት የሚሆኑ ልዩ ልዩ ዕቃዎች፣ ለጠረጴዛ መሸፈኛ፣ የዕቃ መጠቅለያዎች፣ ...ወዘተ/

**293.** በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱና ለቤት ውስጥ ግልጋሎት የሚውሉ ኤሌክትሪካል የሆኑ ወይም ያልሆኑ ዕቃዎች ማምረት /ፍሪጆች፣ ፍሪዘሮች፣ የልብስ ማጠቢያዎች፣ የምግብ መፍጫ ማሽኖች፣ ኩከሮች፣ ...ወዘተ/

**30.**

የቢ

ሮ፣ የሂሳብና የስሌት ማሽኖችን ማምረት

**300.** የቢሮ፣ የሂሳብና የስሌት ማሽኖችን ማምረት /ለቢሮ ሥራ የሚውሉ የማባዣ ማሽኖች፣ የማተሚያ መሣሪያዎች፣ የጽህፈት መኪና፣ የመረጃ ማቀነባበሪያ መሣሪያዎች፣ ...ወዘተ ማምረት/

**31.**

በሌ

ላ ቦታ ያልተጠቀሱ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ማምረት

**311.** በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ማምረት ማለትም የኤሌክትሪክ ሞተር፣ ጀኔሬተር፣ ትራንስፎርመር፣ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ፣ የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች፣ የኤሌክትሪክ ሽቦ፣ ባለልባስና ኬብል ባትሪ፣ የኤሌክትሪክ መብራትና በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የኤሌትሪክ መሣሪያዎችን ማምረት፣

**32.**

ሬዳ

ዮ፣ ቴሌቪዥንና የመገናኛ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ማምረት

**321.**

ሬዲ

ዮ፣ ቴሌቪዥንና የመገናኛ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ማምረት

**33.**

የሕ

ክምና መሣሪያዎች፣ የዓይን መነፅሮች የተለያዩ ካሜራዎችና ሠዓቶችን ማምረት

**331.** የሕክምና መሣሪያዎች፣ የዓይን መነፅሮች፣ የፍቶግራፍ መሣሪያዎች፣ ሠዓቶችን ማምረት፣ የመለኪያ (የመመዘኛ) መሣሪያዎችን ማምረት

**34.**

መ

ኪናዎችና ተሳቢዎችን ማምረት

**341.** መኪናዎችንና ተሳቢዎችን ማምረትና የመኪና መለዋወጫዎችን ማምረት (የመኪና ኤሌክትሪክ ዕቃዎች ማምረትን አይጨምርም - ኮድ 311 ውስጥ ይጠቃለላሉ)

**35.**

ሌሎ

ች የትራንስፖርት መሣሪያዎችን ማምረት

**351.** ሌሎች የትራንስፖርት ዕቃዎችን ማምረት /መርከቦችንና ጀልባዎችን (የስፖርት ጀልባዎችን ጨምሮ) መሥራትና መጠገን፣ ባቡር፣ አውሮፕላን፣ ሞተር ብስክሌት፣ ብስክሌት ማምረት፣ ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ የትራንስፖርት መሣሪያዎችን ማምረት/

**36.**

የቤ

ትና የቢሮ ዕቃዎችን ማምረት፣ በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ምርቶችን ማምረት

**361.** የቤት ዕቃዎችን ለቤተሰብ፣ ለቢሮ፣ ለሆቴል፣ ለምግብ ቤትና ለተለያዩ ድርጅቶች /ሆስፒታል፣ ቲያትር ቤቶች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ ት/ቤቶች፣ ...ወዘተ/ ማምረት፣ የቤት

ዕቃዎች ከድንጋይና ኮንክሪት በስተቀር ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከቀርከሃ፣ ከመስታወት ወይም ከቆዳ የተሠሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም የቤት ዕቃዎቹ ለምግብ ማብሰያ፣ ለሳሎን፣ ለመተኛ፣ ለመቀመጫ፣ ለሥራ ...ወዘተ የሚያገለግሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**362.** ከከበሩ ማዕድናት (ወርቅ፣ አልማዝ ...ወዘተ) ወይም ከአርቲፊሻሎች ጌጣጌጥና የመሳሰሉ ዕቃዎች ማምረት /ሳንቲሞች፣ ሜዳሊያዎች፣ ቅርፃ ቅርፅ ...ወዘተ ማምረት/

**363.**

የሙ

ዚቃ መሣሪያዎች ማምረት

**364.**

የስ

ፖርት ዕቃዎች ማምረት

**369.** ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ምርቶች /እርሳስ፣ እስክሪፕቶና ሌሎች ለጽሕፈትና ለአርት ባለሙያዎች የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣ አሻንጉሊት፣ ጃንጥላ፣ ቁልፍ፣ መጥረጊያ፣ ብሩሽ፣ የአምፖል መሸፈኛ፣ የማስታወቂያ ጽሁፎች፣ ...ወዘተ የመሳሰሉት ማምረት/

## ዋና ክፍል - አራት

## <u>ኤሌክትሪክ፣ ጋዝና ውሃ አቅርቦት</u>

**40.**

ኤለ

ክትሪክ፣ ጋዝ፣ እንፋሎትና ሙቅ ውሃ ማምረት፣ ክምችትና ሥርጭት

**401.**

ኤሌ

ክትሪክ ክምችትና ስርጭት

**402.**

የጋ

ዝ ምርትና ስርጭት

**403.**

እን

ፋሎትና ሙቅ ውሃ አቅርቦት

**41.** ውሃ ማከማቸት፣ ማጣራትና ማሠራጫት

**410፣** ውሃ

ማከማቸት፣ ማጣራትና ማሠራጫት ለምሳሌ ለቤተሰብ፣ ለድርጅቱ ወይንም ለሌሎች

ተቃዋሚዎች በክፍያ ውሃ የማሰራጨት፣ወይም የማከፋፈል አገልግሎት መስጠት፣

## ዋና ክፍል - አምስት

## <u>ኮንስትራክሽን</u>

## 45. ኮንስትራክሽን

451. የኮንስትራክሽን ቦታ ማዘጋጀት /የሕንፃ መሥሪያ ቦታዎች ማጽዳት፣ መጥረግና ማስተካከል/

452. በሙሉ ወይም በግማሽ አጠቃላይ ሕንፃ ሥራ፣ ሲቪል ምሕንድስና ሥራ /አዲስ የሕንፃ ሥራዎች፣ ሙሉ በሙሉ ወይም በግማሽ የመቀየር ሥራዎች፣ ፕሪፋቦችን መገጣጠም፣ እነዚህም መኖሪያዎች፣ መሥሪያ ቤቶች፣ መጋዘኖች፣... መንገዶች፣ ድልድዮች፣ ...ወዘተ ሥራዎችን ያጠቃልላል/

453. በሕንፃዎች የኤሌክትሪክ፣ ውሃና ሌሎች ዕቃዎችን መገጣጠም /ኤሌክትሪክ፣ ውሃ፣ ቴሌፎን፣ አንቴናና ሌሎች ዕቃዎችን መግጠምና እነዚሁኑ ዕቃዎች መጠገንን ይጨምራል/

454. ሕንፃዎችን የማጠናቀቅ ሥራ /ግድግዳና ጣራ ቀለም ቅብ፣ ወለሎችን ታይል፣ ምንጣፍና የመሳሰሉ ማልበስ፣ በግድግዳ ወረቀት ግድግዳዎችን ማስጌጥ፣ ወዘተ/

455. የሕንፃ መሥሪያ መሣሪያዎች ወይም ማፍረሻ መሣሪያዎችን ከሠራተኞች /ባለሙያዎች/ ጋር ማከራየት

# ዋና ክፍል - ስድስት

## የጅምላና ችርቻሮ ንግድ፣ መኪናዎች፣ ሞተር ብስክሌቶች፣ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች መጠገን

## 50. መኪናዎችና ሞተር ሳይክሎች ሽያጭና ጥገና፣ የነዳጅ ችርቻሮ ንግድ

የመኪናዎችና ሞተርሳይክሎች መለዋወጫዎች ሽያጭና ጥገና፣ አሮጌ መኪናዎችን መሸጥ፣ የእጥበት፣ ግሪሲንግና የመሳሰሉ እንዲሁም ነዳጅ በችርቻሮ መሸጥን ያጠቃልላል፡፡ (ነገር ግን የግል መኪና ማከራየት በክፍል 60 የሚመደብ እንጂ በዚህ ክፍል አይካተትም)፡፡

501. የመኪናዎች ሽያጭ

502. የመኪናዎች ጥገና፣ እጥበትና ግሪሲንግ

503. የመኪና መለዋወጫዎች ሽያጭ

504. የሞተር ሳይክሎችና መለዋወጫቸው ሽያጭና ጥገና

505. የተሽከርካሪዎች ነዳጅ ችርቻሮ ንግድ /ለማንኛውም ተሽከርካሪ የሚውሉ ነዳጆችና ቅባቶች ሽያጭ፣ የነጭ ጋዝ ሽያጭም በዚሁ ይጠቃለላል/

**51.**

የጅ

ምላ ንግድና ኮሚሽን ንግድ /መኪናዎችና ሞተር ብስክሌት ንግድን አይጨምርም/

511. በክፍያ ወይም በኮንትራት ስምምነት እንደ ባለቤት ሆነው ጅምላ ሽያጮች /ደላላዎች፣ አጫራቾች፣ በኮሚሽን ወኪሎች፣ ...ወዘተ ባለቤቱን በመወከል ጅምላ ሽያጭ የሚያካሂዱ/

512. የእርሻ ውጤቶች /ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬና አትክልት/ ቁም ከብት፣ ምግብ መጠጥና ትምባሆ ጅምላ ንግድ፣ ሰብል ገበያ ድርጅት

513. የቤት ውስጥ ዕቃዎች ጅምላ ንግድ /የቤት ዕቃዎች፣ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ሰዓቶች፣ የሕክምና ዕቃዎች፣ የግል ንፅህና ዕቃዎች፣ መፃህፍት፣ መጽሔቶች፣ መነፅሮች፣ ጌጣጌጦች፣ የስፖርት ዕቃዎች (ባይስክል ጭምር)፣ ከቆዳ የተሠሩ ዕቃዎች፣ ...ወዘተ ጅምላ ንግድ/

514. ግብርና ነክ ያልሆኑ ምርቶች፣ አሮጌና ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎች /እንደገና የሚሰሩ/ ጅምላ ንግድ /በጠጣር፣ በፈሳሽና በጋዝ መልክ ያሉ ነዳጆችና መሰል ምርቶች፣ ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት፣ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች፣ ጨርቃ ጨርቆችና ከጥቅም ውጪ የሆኑ አሮጌ ዕቃዎች ጅምላ ንግድ/

515. ማሽኖች፣ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ጅምላ ንግድ /ከመኪናዎችና ሞተር ሳይክሎች በስተቀር የኮንስትራክሽን፣ የቢሮ፣ የተለያዩ የጨርቃ ጨርቅ፣ እንጨት፣ ብረትና የመሳሰሉ ኢንዱስትሪዎች ማሽኖችና መሣሪያዎች ጅምላ ንግድ/

519. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች የጅምላ ንግዶች

## 52. ችርቻሮ ንግድ /መኪናና ሞተር ብስክሌቶችን አይጨምርም/፣ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች መጠገን

521. በተወሰነ የንግድ ዘርፍ ባልተሰማሩ ሱቆች፣ መደብሮች ችርቻሮ ንግድ /አዲስና አሮጌ ለግልና ለቤተሰብ ፍጆታ የሚውሉ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን በሱቆች፣ በገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ/

522. የተዘጋጀ ምግብ:- መጠጥና ትምባሆ በተወሰነ የንግድ ዘርፍ በተሰማሩ ሱቆች፣ ገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ፣ ለምሳሌ አትክልትና ፍራፍሬ፣ሥጋና የስጋ ውጤቶች፣እንዲሁም በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ሌሎች ተመሳሳይ ምግብ ነክ የሆኑ የችርቻሮ ንግድ አገልግሎት መስጫዎች በዚህ ይካተታሉ::

523. ሌሎች አዳዲስ ዕቃዎች በተወሰነ ንግድ ዘርፍ በተሠማሩ ሱቆች፣ ገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ /ፋርማሲዎች፣ የሕክምናና የንፅሕና መጠበቂያ ዕቃዎች፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ልብሶች፣ ጫማዎችና የቆዳ ውጤቶች፣ የሕንፃ ቀለሞች፣ ቫርኒሽና የመሳሰሉ፣ የቢሮ ዕቃዎች፣ መጽሐፍት፣ የጽሕፈት መሳሪያዎች፣ የፎቶ ግራፍና የዓይን መነፅር፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ/

524. አሮጌ ዕቃዎችን በሱቆች፣ በገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ

525. በሱቆች፣ በገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ሳይሆን በመንገድ ላይ፣ በገበያ ቦታዎች፣ በጉልቶች፣ በተዕዛዝ፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ፣ የጉሊት ሽንኩርት፣ የጉሊት ጫት፣ የልዋጭ ንግድ፣ የማገዶ እንጨት ንግድ

526. የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች ጥገና /ከማኒፋክቸሪንግ፣ ጅምላ ወይም ችርቻሮ ንግድ ጋር ባልተገናኘ መልኩ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች ጥገና/ ፍራሽና ጫማ እድሳት፣ሰዓትና ራዲዮ አዳሾች

# ዋና ክፍል - ሰባት

# ሆቴሎችና ምግብ ቤቶች

**55.**

ሆቴ

ሎችና ምግብ ቤቶች

551. የመኝታ አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎች፣ የካምፕ ቦታዎችና ሌላ ለአጭር ጊዜ ቆይታ የሚያስተናግዱ የንግድ ቤቶች /ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ የት/ቤት ዶርሚተሪዎች፣ የእንግዳ ቤቶች፣ ሆስቴሎችና መጠለያዎች/

552. ምግብ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ሻይ ቤቶችና ክበቦች፣ ጠላ ቤቶች፣ አረቂ ቤቶች፣ /የመኝታ አገልግሎት አይሰጡም/

## ዋና ክፍል - ስምንት

## ትራንስፖርት፣ የመጋዘን አገልግሎትና መገናኛ

**60.**

የየ

ብስ ትራንስፖርት /ሰው፣ዕቃ ፣በመሬት ላይ ማጓጓዝ/

601. የየብስ ትራንስፖርት (አምቡላንስ አይጨምርም) /የመኪና፣ በሰው/በከብት የሚጎተቱ ጋሪዎች፣ መኪና መከራየት፣ መኪና መንዳት አስተማሪ፣ የሸክም ሥራ ዕቃ ማጓጓዝ (ወዝ አደር)/

**61.**

የው

ሃ ላይ ትራንስፖርት /ሰው፣ ዕቃ፣ በወንዝ፣ በግድቦችና በኃይቆች ላይ ማጓጓዝ/

611.

የው

ሃ ላይ ትራንስፖርት /ሰው፣ ዕቃ፣ በወንዝ፣ በግድቦችና በኃይቆች ላይ ማጓጓዝ/

**62.**

የአ

የር ትራንስፖርት

621.

የአየ

ር ትራንስፖርት

**63.**

ከት

ራንስፖርት ጋር ግንኙነት ያላቸውና አጋዥ ሥራዎች፣ የጉዞ ወኪል

630. ከትራንስፖርት ጋር ግንኙነት ያላቸውና አጋዥ ሥራዎች፣ የጉዞ ወኪል /የካርጎ አገልግሎት፣ የመጋዘን አገልግሎትና ሌሎች የጉዞ ወኪል ሥራዎች/

**64.**

ፖስ

ታና ቴሌኮሙኒኬሽን

641.

የብ

ሔራዊ ፖስታና የፖስታ ወኪሎች አገልግሎት

642. ቴሌ
ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

## ዋና ክፍል - ዘጠኝ

## <u>የፋይናንስ /የገንዘብ እንቅስቃሴ (ዝውውር)</u>

### 65. የፋ
### ይናንስ /የገንዘብ እንቅስቃሴ (ዝውውር)፣ /የመድህንና የጡረታ ዋስትናን አይጨምርም/

**651.** የገንዘብ እንቅስቃሴ (ዝውውር) የሚያካሂዱ ድርጅቶች /ብሄራዊ ባንክና ሌሎች የገንዘብ እንቅስቃሴ ተቋሞች/፣ ቤቶችን ለመሥራት ወይም ለመግዛት ብድር የሚሰጡ የገንዘብ ተቋማት የመሳሰሉት

**659.** ሌሎች የገንዘብ እንቅስቃሴዎች /በጊዜ ገደብ ንብረት በኪራይ የመስጠት፣ ከባንክ አሠራር በተለየ መልክ ብድር መስጠት ...ወዘተ/

### 66. የመድህንና ጡረታ ዋስትና /እንደ ግዴታ የሚሰበሰቡ የማህበራዊ ዋስትናን አይጨምርም/

**660.** የመድህንና ጡረታ ዋስትና /የህይወት፣ የንብረትና ሌሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ ዋስትናዎች፣ በጡረታና ዋስትና ኮሚሽን የሚደረገውን እንቅስቃሴ አይጨምርም/

### 67. ከፋ
### ይናንስና መድህን እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች

**671.** ከፋ
ይናንስና መድህን እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች

## ዋና ክፍል - አሥር

## <u>የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ ኪራይና ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎች</u>

### 70. የማ
### ይንቀሳቀስ ንብረት የተመለከቱ እንቅስቃሴዎች

**701.** የማይንቀሳቀስ ንብረት የተመለከቱ እንቅስቃሴዎች፣ ኪራይ ቤቶች አስተዳደር

### 71. ማሽኖችና መሣሪያዎችን ያለ ኦፐሬተር ማከራየት፣ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ማከራየት

**711.** ማሽኖችንና መሣሪያዎችን ያለ ኦፐሬተር ማከራየት /የትራንስፖርት፣ የግብርና፣ የኮንስትራክሽን፣ የቢሮ (ኮምፒዩተር ጭምር) እና ሌሎች ማሽኖችና መሣሪያዎች ያለ ኦፐሬተር ማከራየት/

713. ለግለሰብና ለቤት ውስጥ ግልጋሎት የሚውሉ በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ዕቃዎችን የማከራየት አገልግሎት ለምሳሌ ብስክሌት፣ ጆተኒ፣ ቪዲዮ ቴፖችን፣ሪኮርደሮችን ጌጣጌጦችን፣ ጋዜጣና መፅሔት እና የመሳሰሉት የማከራየት አገልግሎት መስጠት፣

## 72. ኮምፒዩተርና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎች

721. ሐርድ ዌርን በተመለከተ ምክርና እገዛ መስጠት

722. ሶፍት ዌርን በተመለከተ ምክርና እገዛ እንዲሁም አቅርቦት

723. መረጃ በኮምፒዩተር ማቀነባበርና ተመሳሳይ ሥራዎች

724. የቢሮ፣ የሂሳብና የኮምፒዩተር ማሽኖች ጥገና

729. ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ ተመሳሳይ የኮምፒዩተር ሥራዎች

## 73. ምርምርና ልማት:- በመንግስት አስተዳደር ሥራ የሚንቀሳቀሱ የምርምርና የልማት ሥራዎችን አይጨምርም/

731. በተፈጥሮ ሳይንስና በምህንድስና ላይ የተመረኮዘ ምርምርና ቤተ ሙከራዎች

732. በሶሻል ሳይንስ፣ በቋንቋ፣ በባህልና በመሳሰሉት ላይ የተመረኮዘ ምርምሮችና ቤተሙከራዎች

## 74. ሌሎች የንግድ ሥራዎች

741. ሕግ ነክና የጥብቅና ሥራዎች፣ የሂሳብ፣ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ንግድ ሥራዎች፣ ስለታክስ አማካሪዎች፣ የገበያ ጥናትና የሕዝብ አስተያየት አሰባሳቢዎች፣ የንግድና የአስተዳደር ሥራዎች አማካሪዎች /ኮንስለንታንሲ/ የቀረጥ አማካሪ

742. አርክቲክቸራል፣ የምሕንድስናና ሌሎች የቴክኒክ የማማከር ሥራዎች፣ የዕቃዎችና ምርቶች ኢንስፔክሽን/ቴስቲንግ (ከህክምና መሣሪያዎች በስተቀር)

743. የማስታወቂያ ሥራዎች /በጋዜጦች፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢግዚቢሽን፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ ...ወዘተ የማስተዋወቂያ ሥራዎች/

749. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች የንግድ ሥራዎች /ማንኛውንም የመኖሪያና የሥራ ቦታ ሕንፃዎች ጽዳት ሥራ፣ የፎቶ ማንሳትና ማጠብ ሥራ፣ የማሸግ /የሕክምና የውበት መጠበቂያና የመሳሰሉትን ዕቃዎች ማሸግ፣ ስም መለጠፍ ... ወዘተ/ ሥራዎች፣/ ሠራተኛን ከአሰሪ መቅጠር፣ ሌሎች የድለላ ሥራዎች የማጫረት ሥራ፣ የመተርጎም ሥራ፣ የኤግዚቢሽን ሥራ፣ ታይፕ የማድረግና የማረም ሥራ፣ የፋሽን ዲዛይን ማዘጋጀት

# ዋና ክፍል - አሥራ አንድ

## የመንግስት አስተዳደርና የመከላከያ፣ የማህበራዊ ዋስትና (ጡረታ) አገልግሎት

**75.**

የመ

ንግስት አስተዳደርና መከላከያ፣ የማህበራዊ ዋስትና (ጡረታ) አገልግሎት

**751.** የመንግስት አስተዳደር፣ የሕብረተሰቡን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች የሚቀይሱ የመንግስት ድርጅቶች /በማዕከልና በተዋረድ የተቋቋሙ እስከ ቀበሌ ድረስ የመንግስት የሚኒስቴር፣ ኮሚሽንና መሰል መሥሪያ ቤቶች፣ የታክስና መሰል ሥራዎችን የሚሰሩ እንደ አገር ውስጥ ገቢና የመሳሰሉ ድርጅቶች፣ የሕብረተሰቡን የትምህርት የጤና፣ የባሕልና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚከታተሉና የሚያካሂዱ መ/ቤቶችና መሰል የመንግስት ድርጅቶች/

**752.** ሁሉን አቀፍ ግልጋሎት ለህብረተሰቡ የሚሰጠ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ለምሳሌ /የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የፖሊስና የሕብረተሰቡን ደህንነትና ሥርዓት የመጠበቅ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ ፍርድ ቤቶች፣ እሥር ቤቶች፣ ...ወዘተ

**753.** የጡረታና ዋስትና አገልግሎት /የመንግሥት ጡረታና ዋስትና ኮሚሽን፣ የህመም የአደጋና የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ አገልግሎትን ያካትታል፡፡ (ነገር ግን ሌሎች በእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የሚሰጡ እርዳታዎች በክፍል 853 እንጂ በዚህ ክፍል አይመደቡም)

# ዋና ክፍል - አሥራ ሁለት

## የትምህርት፣ የጤና ማህበራዊ አገልግሎት

**80.** ትምህርት /የግልና የመንግስት ት/ቤቶችንና በቀንም ሆነ በማታ ትምህርት የሚሰጡትን ያጠቃልላል/

**801.** የአንደኛ ደረጃ ትምህርት/የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የመዋዕለ ሕፃናት የሕፃናት ማሳደጊያ ፕሮግራሞችና፣ ወደ አንደኛ ደረጃ ለመግባት የሚያዘጋጁ በዚሁ ይጠቃለላሉ/

**802.** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት/የመለስተኛ፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ለየት ባለ መልክ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችም በዚሁ ይጠቃለላሉ/

**803.** የከፍተኛ ትምህርት/ሁለተኛ ደረጃ በላይ ለዩኒቨርስቲ ትምህርት /ዲግሪ ወይም ዲፕሎም የሚያስገኙ/ የሚያዘጋጁ ት/ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች/

**804.** የመሠረተ ትምህርት ሌሎች መደበኛ ያልሆኑ ትምህርቶች /የመሠረተ ትምህርት፣ የሙያና የቴክኒክ ትምህርት በቀን ወይም በማታ በት/ቤቶች ወይም በተለያዩ ተቋማት ወይም በተልዕኮ ወይም በሬዲዩ፣ በቴሌቪዥን ትምህርት የሚሰጡ ፕሮግራሞች፣ በመደበኛ ትምህርት ሊተረጎም የማይችል እንደ ቄስ፣ ቁርዓን፣ ...ወዘተ ትምህርቶች በሙሉ በዚህ ይጠቃለላሉ፡፡/

**85.**

ጤ

ናና ማህበራዊ ሥራ

**851.** የሰዎች ጤና የመጠበቅ አገልግሎት /ሆስፒታሎች፣ የጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች፣ /በድርጅቶች፣ ት/ቤቶች፣ ...ወዘተ ውስጥ ያሉትንም ያጠቃልላል፣/ የአምቡላንስና ሌሎች ግልጋሎቶችን የሚሰጡ እንደ ቀይ መስቀል የመሳሰሉት ድርጅቶች፣ የባህል ሕክምናዎች/ የመከላከያ ሕክምና ሥራዎችን አያጠቃልልም፡፡

**852.** የእንስሳት ሕክምና /የቬትሪናሪ አገልግሎት፣ በእርሻ ቦታዎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ...ወዘተ የእንስሳት ሕክምና አገልግሎት/

853. የማህበራዊ ሥራ /በመጠለያዎች ወይም ከመጠለያ ውጭ የተለየ እንክብካቤ ለሚፈልጉ የማህበረሰብ አባላት ለምሳሌ ለማየት ለተሳናቸው፣ ለመስማት ለተሳናቸዉ፣ ለአእምሮ በሽተኞች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለሕፃናት ለአረጋዊያን ተጧሪዎች፣ ...ወዘተ ማህበራዊ እገዛ የማድረግ አገልግሎት መስጠት በተጨማሪም በመጠለያ ጣቢያዎች፣ የስደተኛ ካምፖች፣ ችግሮቹ ባሉበት ቦታ፣ ...ወዘተ በተለያዩ የመንግስት የግልና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ምክር፣ እገዛና ሌሎች ማህበራዊ እርዳታዎችን መስጠት ለምሳሌ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን፣ ወርልድ ቪዥን፣ ኬር፣ ኤስ ኦኤስ፣ ዝዋይ የሕፃናት አምባ፣ ...ወዘተ/

# ዋና ክፍል - አሥራ ሦሥት

## ሌሎች የማህበራዊ፣ የባህል፣ የመዝናኛ የግልና የቤተሰብ ግልጋሎቶች

90.

የቆ

ሻሻ ማስወገጃና ንጽሕና አገልግሎቶች

900. የቆሻሻ ማስወገጃና ንጽሕና አገልግሎቶች/ከቤተሰብ፣ ከኢንዱስትሪዎች፣ ከንግድ ተቋሞችና ከመሳሰሉ ቆሻሻ መሰብሰብ፣ ማንንዝና /በመኪና፣ በቱቦ ወይም በሌላ መልክ ሊሆን ይችላል/ ማስወገድ/

91.

በሌ

ላ ቦታ ያልተጠቀሱ የሙያ፣ የንግድና የሠራተኛ ማህበራት እንቅስቃሴዎች

911. የንግድ የሥራና የሙያ ማህበራት ሥራዎች /የኢትዮጵያ ንግድ ም/ቤት፣ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ማህበር፣ የኢትዮጵያ ኬሚስትሪ ባለሙያዎች ማህበር፣ ...ወዘተ የመሳሰሉ

912. ሥራና ሠራተኛን የሚመለከቱ ማህበራት እንቅስቃሴዎች /የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር፣ በአንድ ሙያ ወይም የሥራ ዘርፍ የተሠማሩ ባለሙያዎችን ወይም ሠራተኞችን ጥቅም ለማስጠበቅ የተቋቋሙ ማህበራት/

919. ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ የሙያና መሰል ማህበራት /የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የወጣት ማህበራት፣ ሌሎች በባሕልና በስፖርት፣ በተለያዩ የመዝናኛና ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ማህበራትና ክበቦች/

92.

የመ

ዝናኛ፣ የባሕልና የስፖርት እንቅስቃሴዎችን

921. የሲኒማ፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና የመሳሰሉ የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ማዘጋጀት /በምስል የተቀነባበሩ ቲያትር፣ ሲኒማ፣ ...ወዘተ በቲያትር ቤቶች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ማሠራጫት፣ የቪዲዮ ቴፖች ጥናታዊ ፊልም፣ ...ወዘተ ለድርጅቶች (ለግለሰቦች ማከራየትን አይጨምርም) ማሠራጨትና የመሳሰሉ የመዝናኛ አገልግሎቶች/ ናይት ክለብ ዋና ሥራቸው የሆነ

922. የዜና ስርጭት ድርጅቶች /ዜናዎችና ምስሎችን ለሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና ለመሳሰሉት ማቀበል ወይም ማቅረብ/

923. የቤተመጽሐፍ፣ ሙዝየምና ተመሳሳይ ማህበራዊ አገልግሎቶች

924. የስፖርትና ሌሎች የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች /የእግር ኳስ፣ የቴኒስ፣ የዋና፣ የቦክስ፣ ቼዝ፣ ...ወዘተ ክለቦችና ድርጅቶች፣ በተጨማሪም የስፖርት አሰልጣኞች፣ ሠዓት ተቆጣጣሪዎች፣ ዳኞች፣ ...ወዘተ ሥራዎች:/

93.

ሌለ

ች አገልግሎቶች

930. ሌሎች አገልግሎቶች፣ ላውንድሪ፣ ሊስትሮ፣ የመኪና መጠበቅ፣ የታክሲ ወያላ፣ የመኪና ረዳት /የእጥበት (ሳዉና ... ወዘተ)፣ የፀጉርና ሌሎች የቁንጅና መስጫዎች፣ የቀብር ስነ-ሥርዓት አስፈፃሚዎች ...ወዘተ እና በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ሌሎች የባሕል፣ የመዝናኛና የስፖርት አገልግሎቶች፣ ዕቃ የማውረድና የመጫን

931. በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የቀን ሠራተኞች፣የጉልበት ሥራ/ሸክም/ አገልግሎት መስጠት፣

# ዋና ክፍል - አሥራ አራት

## ቅጥር ሠራተኞች ያሏቸው ቤተሰቦች

95. ቅጥር ሠራተኞች ያሏቸው ቤተሰቦች

950. ቅጥር ሠራተኞች ያሏቸው ቤተሰቦች /ለቤት ውስጥ ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች ለምሳሌ የቤት ሠራተኞች፣ የቤት ዘበኞች፣ አስተናጋጆች፣ ሞግዚቶች፣ የቤተሰብ ሾፌሮች፣ ...ወዘተ ያሏቸው ቤተሰቦች/

# ዋና ክፍል - አሥራ አምስት

## የውጭ ድርጅቶች

99. የውጭ ድርጅቶች

990. የውጭ ድርጅቶች /የተባበሩት መንግሥታት፣ የአህጉር አቀፍና ሌሎች የትብብር ድርጅቶች ለምሳሌ ኢሲኤ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ የአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ የነዳጅ አምራችና ላኪ አገሮች ድርጅት፣ ...ወዘተ/

# ተጨማሪ ማብራሪያዎች

### በዓምድ 31 እና ዓምድ 32 ስለሚሰጡ የተወሰኑ ኮዶች ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ

### 1ኛ የዋና ሥራ ዓይነት

741:- ያመረቱትን እህል መፍጨት (ፈጭቶ ዱቄቱን መሸጥ)፣ ቆሎ መፋቅ፣ መቁረጥ፣ ፍቆ (አዘጋጅቶ) መሸጥ፣ ቅቤ፣ አይብና የመሳሰሉትን አውጥቶ (አዘጋጅቶ) ሻጮች:: ምግብ፣ ጠላ፣ አረቄ አዘጋጅቶ መሸጥ፣ ትምባሆ አዘጋጅቶ መሸጥ፣ ጭማቂ አዘጋጅቶ መሸጥ፣ ጀላቲና የመሳሰሉት ጣፋጭ ምግቦች ማዘጋጀት (አዘጋጅቶ መሸጥ):: የከብት ቆዳ ገፋፊዎች::

921:- ኩበት፣ ቅጠል፣ እንጨት፣ ጫት፣ ቡና እና ሌሎች ተመሳሳይ የግብርና የደን ምርቶችን ለቃሚ፣ ፣ ለቅሞ መሸጥ እንዲሁም እንጨት መቁረጥ፣ ቆርጦ መሸጥ፣ ሳር ማጫድ፣ አጫጅ፣ አጭዶ መሸጥ በማለትና በተመሳሳይነት የተጠቀሱ የዋነኛ ሥራ ዓይነቶች

524:- (አዲስ) በግል የሚተዳደሩ ነጋዴዎች ቀጣሪ ከሆኑ ወይም ከ10 በላይ የሥራ ተካፋይ ሠራተኞች ካሏቸው::

### 2ኛ የድርጅት ዋነኛ ምርት

020: - እንጨት ለቅሞ የመሸጥ አገልግሎት

- እንጨት ቆርጦ መሸጥ

- ሳር አጭዶ መሸጥ

**011: - ቡና፣ ጫት ለቅሞ የመሸጥ አገልግሎት**

**012: - ኩበት ለቅሞ የመሸጥ አገልግሎት**

**713 (አዲስ):- ብስክሌት፣ ሞተር ብስክሌት፣ ጀተኒ፣ ሌሎች የመዝናኛ (የመጫወቻ) ወይም የስፖርት ዕቃዎችን የማከራየት አገልግሎት**

**931 (አዲስ):- የቀን ሠራተኞች:- በግል የጉልበት ወይም የሸክም ሥራ በመሥራት የሚተዳደሩ (ሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ)**

**ማሳሰቢያ:**

**ከማምረት (ማዘጋጀት) እስከ መሸጥ ድረስ ለተጠቀሱ የዋነኛ ሥራ ወይንም የድርጅት ዋነኛ ምርቶች፣ በዓምድ 31 ላይ ለማምረት (ማዘጋጀት) ቅድሚያ ተሰጥቶ ከዚሁ ጋር የተገናዘበ የዋነኛ ሥራ ዓይነት ኮድ እንዲሰጥ::**